የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2

1) ከሚከተሉት ውስጥ የማቴዎስ ወንጌልን ስለጻፈው ሰው ትክክል የሆነው የትኛው ነው
ሀ) የቀድሞ ስሙ ሌዊ ሲሆን የጌታ ሐዋርያ ከመሆኑ በፊት ቀራጭ ነበር
ለ) በአስቆሮይቱ ይሁዳ ምትክ የተተካ ሐዋርያ ነው
ሐ) ሐዋርያ ሳይሆን ጌታን እየተከተሉ ይማሩ ከነበሩ አርድዕቶች መካከል አንዱ ነበር
መ) ጌታችን ካረገ በኋላ የተነሳ ሐዋርያ ነው

2) የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት የሚለየው በምንድን ነው?
ሀ) ስለ ሰብአ ሰገል ወደ ጌታችን መምጣት የተጠቀሰበት መሆኑ
ለ) የጌታችንን የዘር ሐረግ በዝርዝር ማስቀመጡ
ሐ)ቤተልሔም ስላሉ ሕጻናት መገደል እና ስለ ጌታችን ስደት ማንሳቱ
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

3) የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊው ዮሴፍ እመቤታችንን በስውር እንዳይተዋት ባረጋጋው ጊዜ ሕጻኑን ማን ትለዋለህ አለው?
ሀ) ኢየሱስ ለ) አማኑኤል ሐ) ክርስቶስ መ)ሁሉም

4) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት ከተማ ተወለደ?
ሀ) ገሊላ ለ) ናዝሬት ሐ) ቤተልሔም መ) ኤፍራታ ሠ) ሐ እና መ ረ) ሀ እና ሐ

5) እመቤታችን ከስደት እንድትመለስ ምክንያት የነበረው የቱ ነው?
ሀ) ያሳድዳቸው የነበረው የንጉስ ሄሮድስ መሞት
ለ) በአውግስጦስ ቄሣር ትዕዛዝ መሰረት በይሁዳ አውራጃ ያለው ሰው በሙሉ እንዲቆጠር ወደ ቤተልሔም ከተማ እንዲመጣ መደረጉ
ሐ) አባቱ በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ መንገሱ
መ) መልሱ የለም

6) ከግብፅ ስደት መልስ አረጋዊው ዮሴፍ ሕጻኑን እናቱን ይዞ ለመኖር ወደየት ከተማ ሄደ?
ሀ) ቤተልሄም ለ) ይሁዳ ሐ) ገሊላ ናዝሬት መ) ቤተሣይዳ

7) ለዮሴፍ በሕልሙ 'ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና፥ተነሣ፥ሕፃኑንና እናቱንም ይዘኽ ወደ ግብጽ ሽሸ፥እስከነግርኽም ድረስ በዚያ ተቀመጥ' ብሎ የነገረው መልአክ የቱ ነው?
ሀ) ቅዱስ ሚካኤል ለ) ቅዱስ ገብርኤል ሐ) ቅዱስ ኡራኤል መ) ቅዱስ ሩፋኤል ሠ) ቅዱስ ፋኑኤል

8) ከሚከተሉት ውስጥ ሰብአ ሰገል ለጌታችን እጅ መንሻ ካቀረቡት ውስጥ እይካተትም?
ሀ) ወርቅ ለ) ብር ሐ) ከርቤ መ) እጣን

9) "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት" የሚለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እና በእመቤታችን ስደት ላይ የተነገረው ትንቢት በየትኛው ነቢይ የተነገረ ነው?
ሀ) ኤርምያስ ለ) ኢሳይያስ ሐ) ሆሴዕ መ) ዘካሪያስ

10) ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ድረስ ያለው የዘር ሃረግ ብዛት _____ ትውልድ ነው።
ሀ) ዐሥራ አራት ለ) ሃያ ስምንት ሐ) አርባ ሁለት መ) ሰባ ስምንት

11) የማቴዎስ ወንጌል ስንት ምዕራፎች አሉት?
ሀ) ሃያ ሁለት ለ) ሠላሳ ሐ) ሃያ መ) ሃያ ስምንት

12) ከጌታችን የዘር ሃረግ ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የምትመደበው ሴት ማን ናት?
ሀ) ራኬብ ለ) ሩት ሐ) ትዕማር መ) ዛራ

13) ከሚከተሉት ውስጥ በትውልድ ቅደም ተከተል የትኛው ይቀድማል?
ሀ) አሚናዳብ ለ) ይስሐቅ ሐ) ዳዊት መ) ቦኤዝ

14) ሰብአ ሰገል ወደ ጌታችን ከሩቅ ምሥራቅ በምን እየተመሩ መጡ?
ሀ) በኮከብ ለ) በመልዓክ ሐ) በራዕይ መ) በግመል

15) ከያዕቆብ ልጆች ውስጥ የጌታችን የዘር ሃረግ ተዋረድ የመጣው በየትኛው ነው?
ሀ) ይሁዳ ለ) ሮቤል ሐ) ብንያም መ) ሌዊ ሠ) ዮሴፍ

16) 'ድምፅ በራማ ተሰማ፥ ልቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፥ መጽናናትም አልወደደችም፥ ልጆቿ የሉምና' ብሎ ትንቢት የተናገረው ነቢይ ማን ነው?
ሀ) ኢሳይያስ ለ) ሕዝቅኤል ሐ) ኤርሚያስ መ) ሆሴዕ

17) ታላቁ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በርሱ ምትክ የነገሰው ንጉስ የቱ ነው?
ሀ) አርኬላዎስ ለ) አግሪጳ ሐ) ጢባርዮስ ቄሳር መ) ታናሹ ሄሮድስ

18) "አንቺ ቤተልሔም ከይሁዳ አለቆች ከቶ አታንሺም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ ከአንቺ ይወጣልና" የሚለው ትንቢት በየትኛው ነቢይ የተነገረ ነው?
ሀ) ዘካርያስ ለ) ኤርምያስ ሐ) ሚክያስ መ) ሆሴዕ

19) ሄሮድስ ኢየሱስ ክርስቶስ የት እንደሚወለድ እንዴት አወቀ?
ሀ) ሰብአ ሰገል ነግረውት
ለ) ከካህናት አለቆች የሕዝቡንም ጸሓፎች ጠይቆ
ሐ) መጀመሪያውኑም የት እንደሚወለድ ያውቅ ነበር
መ) መጻሕፍትን አንብቦ

20) የእመቤታችን ለዮሴፍ መታጨት ለምን አስፈለገ?
ሀ) ጌታ የመፀነሱን ምስጢር ከኢጋንንት ለመሰወር
ለ) ለመናፍቃን ክህደት ምክንያት እንዳይሆን
ሐ) ዘመዷ ስለሆነ በእርሱ እመቤታችን ክርስት(ከዘር) ጉበታ እንድትቆጠር
መ) ሁሉም